# የሸካ ደን

## የሸካ ደንን አስመልክቶ በተለያዩ ባለሙያዎች የተደረገው ጥናት ዋና ዋና ነጥቦች

ማጠቃለያ፡- ታደሰ ወ/ማርያም (PhD)
ማስረሻ ፈጠነ (Prof.)

ትርጉም፡- ዮናስ ገብሩ

በመልካ ማህበር የተዘጋጀ

© ይህን መጽሐፍ ያለማህበሩ ፈቃድ ማባዛትም ሆነ ለሌላ አገልግሎት መጠቀም የተከለከለ ነው።

መልካ ማህበር
የመ.ሣ.ቁጥር 1519 ኮድ 1250
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ +251 11 550 71 72
ፋክስ +251 11 550 71 72
E-Mail: melca@ethionet.et
Website: www. melca-ethiopia.org

ማስታወሻ፣
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሃሣቦች በሙሉ የአጥኚዎች መሆኑንና የግድ የመልካን አስተሳሰብ የሚያንፀባርቁ አለመሆናቸውን እናስታውቃለን።

## ማውጫ

መልዕክት ................................................................................. i
ምስጋና ...................................................................................iii
ጥናቱን ያካሄዱት ...................................................................... iv

በመልካ ማህበር አስተባባሪነት በ1999 ዓ.ም. በሸካ ደን
ላይ የተደረገ ዘርፈ ብዙ ጥናቶች አጠቃላይ ውጤት ....................... 1
አጠቃላይ መግለጫ ..................................................................... 1
1. መግቢያ ............................................................................. 6
2. የጥናቱ መነሻ ........................................................................ 7
3. የጥናቱ ስፋት/ጥልቀት ........................................................... 10
4. ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ እና የአጠናን ዘዴ ................................ 11
   4.1 ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ/ክልል ........................................ 11
   4.2 የአጠናን ዘዴ ................................................................ 12
5. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች ...................................................... 14
   5.1 የመሬት ሽፋን/ገጽታ ለውጥን በተመለከተ ........................ 14
   5.2 ብዝሐ ህይወትና የመሬት ሽፋን መለዋወጥ ..................... 17
   5.3 ባህልና የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ....................................... 19
   5.4 ህጋዊና ተቋማዊ ሥርዓት ............................................... 22
   5.5 ከሸካ ደን የሚገኘው ጥቅም/እሴት .................................. 28
6. ማጠቃለያ ........................................................................... 30
7. የመፍትሔ ሃሣቦች ................................................................ 32

# መልዕክት

"Forests of Sheka" በሚል የታተመው የአምስት ባለሙያዎች ጥናት ውጤት የሆነውን መጽሐፍ ካሳተምን በኋላ የሸካ ጐሳ መሪዎችን ጨምሮ ሌሎች ሰዎች በጠየቁት መሠረት ነው የመጽሐፉን ማጠቃለያ ተርጉመን ለማቅረብ የወሰንነው፡፡ በዚህች ማጠቃለያ ውስጥ ከተካተቱት ጭብጦች መሐከል አሁን የተለወጡ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ የሸካ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ የመንግሥት አካላት የበለጠ ማህበረሰቡ ለደኑ ያለውን መብት ያውቃሉም፤ ያስከብራሉም፡፡ ኢንቨስትመንት ከበፊቱ በተሻለ መልኩ በጥንቃቄ ይከናወናል፡፡ የአካባቢው ማህበረሰቦች በተሻለ መልኩ ደኑን ለመንከባከብ እየተንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ የአካባቢው ወጣቶች በተለይ በማሻና በአንደራቻ በመሰማራት ለአካባቢው ነዋሪ ትምህርት እየሰጡ ናቸው፡፡ እኛም እንደመልካ ስለደኑና ስለህብረተበሱ ባህል ያለን እውቀት እየጨመረ ነው፡፡

ከአባባቢው ማህበረሰብ፣ የጐሳ መሪዎች፣ የሃይማኖት መሪዎችና የመንግሥት አካላት ጋር በመመካከር እየሠራን እንገኛለን፡፡ ሸካን እንደመነሻ በማድረግ የሸካ ደን ጥምረት /Sheka Forest Alliance/ ከሚል የ13 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስብስብ ጋር ደንና የማህበረሰቦች መብትን በተመለከተ በትብብር እየሠራን ነው፡፡ በዚህም የተወሰነ ለውጥ እየተገኘ ነው፡፡

ይህ ማለት በደኑ ላይ ጫና የለም ማለት አይደለም፡፡ ትግሉ በአንድ በኩል የሸካ ደንን እንደተፈጥሮ ሃብት ብቻ በማየት እየቆረጡ መጠቀምን፣ ጫካውን ወደ ሌላ እርሻ አይነት (ለምሳሌ ለቡናና ለሻይ ተክል) ማድረግን ወይንም ሌላ ዓይነት አጠቃቀምን በሚያራምዱና በሌላ በኩል ደኑን እንደአምልኮ ቦታ፣ እንደሕይወታቸው፣ እንደማር ምንጫቸው እንደልብሳቸው በሚያዩና ይህንንም በሚደግፉ መሐከል የሚደረግ ሽኩቻ ነው፡፡ ማንም የሸካ ነዋሪ ሕይወቱ እንዳይሻሻል የሚፈልግ የለም፡፡ ትልቁ ጥያቄ እንዴት የሚለው ነው፡፡ የመልካ አመለካከት ደኑን ከማጥፋት ይልቅ ሌላ አማራጮች አሉ የሚል ነው፡፡

አሁን ቆም ብለን ካላሰብን በኋላ ልንመልሰው ወደማንችለው አቅጣጫ እንሄዳለን። የደን ሽፋኑ ከ2.5% በታች በሆነበት አገር ተቀምጠን በሸካ ደን መፍረድ አንድ ዓይን ኖሮን በአፈር ከመጫወት ይቆጠራል። በዓለም የከባቢ አየር ለውጥ ምክንያት የደን ዋጋ እየጨመረ ነው። የሸካ ደን ትልቅ የካርቦን ዳይ ኦክሳይድ ጐተራ ነው። ይህንን በማጉላት ወደፊት ለማህበረሰቡ የሚተርፍ ፋይዳ ማምጣት እንችላለን። እጅግ በጣም የሚያምር ቦታ በመሆኑ በቀላሉ በጥናት ለተመረኮዘ ኢኮ ቱሪዝም ልናውለው እንችላለን። ህብረተሰቡ ማሩን ራሱ እንዲያዘጋጅና ለሰዎች እንዲሸጥ በማድረግ ገቢውን እንዲያሻሽል ልናደርግ እንችላለን። ብዙ አማራጮች አሉን።

ስለዚህ ሁላችንም ህብረተሰቡን ባማከረ እና ባማከለ አካሄድ የሸካ ደን የወደፊት ሁኔታ እንዲወሰን መታገል እንዳለብን አምናለሁ። ይህች መጽሐፍም ለዚህ እንቅስቃሴ በትንሹም ቢሆን አስተዋጽኦ እንደምታደርግ ተስፋ አደርጋለሁ።

ሚሊዮን በላይ
የመልካ ማህበር ዳይሬክተር

# ምስጋና

መልካ ማህበር በሸካ ደን ሁኔታ ላይ የተደረገውን የጥናት ውጤት "የሸካ ደን" በሚል ርዕስ በመጽሐፍ መልክ ለአንባቢያን ሲያቀርብ ደስታ ይሰማዋል።

ይህ መጽሐፍ እውን እንዲሆን ከጥናት ጽሑፍ መረጣ፣ አጥኚዎችን ከመመልመልና ከማማከር አልፎ የጥናቱ ውጤት ለአንባቢያን ከመድረሱ በፊት ተገቢ የሆነ አስተያየት በማቅረብ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉልንን አቶ ንጉሡ አክሊሉ ከአካባቢ ተቆርቋሪዎች መድረክ እንዲሁም አቶ ማንያውቃል መኮንን ከኦርጋናይዜሽን ፎር ሶሻል ጀስቲስ ከልብ እናመሰግናለን።

የጥናት ውጤቱ ለሚመለከታቸው አካላት በሚቀርብበት ወቅት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የተባበሩንን የሸካ ደንን ለመጠበቅ የተቋቋመው የዘጠኝ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጥምረት "Sheka Forest Alliance" አባላት የሆኑትን እናመሰግናለን።

ጥናቱ በሸካ ዞን በሚካሄድበት ወቅት ተገቢውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩን የሸካ ዞን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የጐሣ መሪዎችና ግለሰቦች በሙሉ እናመሰግናለን። እንዲሁም የጥናት ቡድኑ ሸካ ዞን በሄደበት ወቅት ማረፊያ ቦታ በማዘጋጀትና መጓጓዣ በማቅረብ ለተባበሩን የ"Non-Timber Forest Product (NTFP)" ድርጅትን በጣም እናመሠግናለን።

በሸካ ደን ላይ የተደረገውን ጥናት ወጪ በመሸፈንና የጥናት ውጤቱ ረቂቅ ላይ እርማትና አስተያየት በመስጠት የተባበረንን "ABN/Gaia Foundation" እንዲሁም ከዚሁ ድርጅት ጋር በመተባበር የሕትመቱን ወጪ ለሸፈኑልን የ"Henrich Boell Foundation" የከበረ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

በመጨረሻም በተለያየ መልክ ለዚህ መጽሐፍ ታታሞ መውጣት ለተባበሩን፣ ለመጽሐፉ ጥናት አቅራቢዎችና መጽሐፉ የመጨረሻ መልኩን እንዲይዝ ያደረጉትን አርታኢ ፕሮፌሰር ማስረሻ ፈጠነን ከልብ እናመሰግናለን።

## ጥናቱን ያካሄዱት

1. አሰፋ ስዩም (አቶ)
   Ethiopian Agricultural Economics Society
   E-mail: aseyoumw@yahoo.com

2. በድሩ ሸረፋ (PhD)
   Dresden Technical University
   E-mail: bedrry@yahoo.com

3. ማስረሻ ፈጠነ (Prof.)
   Department of Biology, A.A University
   E-mail: mfetene@bio.aau.edu.et

4. መለሰ ዳምጤ (አቶ)
   Ethiopian Civil Service College
   E-mail: melesd@yahoo.com

5. ሙሐሙድ አብዱላሂ (አቶ)
   Ethiopian Civil Service College
   E-mail: mohabub@yahoo.com

6. ታደሰ ወ/ማርያም (PhD)
   Faculty of Education, A.A. University
   E-mail: twgole@ethionet.et

7. ዘውዴ ጆቴ (አቶ)
   Ethiopian Coffee Forest Forum
   E-mail: Zewdiejote@yahoo.com

## በመልካ ማህበር አስተባባሪነት በ1999 ዓ.ም በሸካ ደን ላይ የተደረጉ ዘርፈ ብዙ ጥናቶች አጠቃላይ ውጤት

የመልካ ማህበር መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው። ዓላማው ከተፈጥሮ ጋር ዘለቄታዊ ግንኙት ያላቸው ባህላዊ እሴቶቻችን እንዲያንሰራሩ ማድረግ ነው። ከዚህ ዓላማ በመነሳት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሸካ ዞን በሚገኙ በማሻና አንደራቻ ወረዳዎች ዘርፈ ብዙ የሆኑ ባለሙያዎችን በማሠማራት የሸካ ደን ያለበትን ሁኔታ በሳይንሳዊ መረጃ በማስደገፍ መረጃ ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል። በዚህም ጥናት የህግ አግባቦችን፣ማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን፣ ስነ ምህዳራዊና እንዲሁም የብዝሐ ህይወት ስርጭትን ለመዳሰስ ተሞክሯል። የአጥኚ ቡድኑ አባላት ያቀረቡት የጥናት ውጤት በእንግሊዝኛ ቋንቋ "Forests of Sheka" በሚል ርዕስ በመጽሐፍ መልክ ታትሞ የቀረበ ሲሆን፤ ከመጽሐፉ ውስጥ የጥናቱን አጠቃላይ ጭብጥ የሚገልፀውን ክፍል በአማርኛ በማስተርጎም ለሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በሸካ ዞን ለሚገኙ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ይደርስ ዘንድ ከዚህ በሚከተለው መልኩ አቅርበንላችኋል።

### አጠቃላይ መግለጫ

ይህ ሪፖርት በመሬት አጠቃቀም መለዋወጥ ሳቢያ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሸካ ዞን ማሻና አንደራቻ ወረዳዎች ውስጥ የታየው የመሬት አጠቃቀም ለውጥ በአካባቢ፣ በተፈጥሮ ሀብትና በህብረተሰቡ ኑሮ ላይ የታየውን ለውጥ የዳሰሰ የዘርፈ ብዙ ጥናቶች ጭብጥ ድምር ውጤት ነው። ጥናቱ ከሳተላይት የተወሰዱ ምስሎችን፣ የተለያዩ ዕፅዋት ዝርያዎችን ቅኝት፣ ባህላዊና ተለምዶአዊ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ሁኔታዎችን እና ህጋዊና ተቋማዊ አደራጃጀቶችን እንዲሁም ደግሞ ከደን ሊገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከሌላ አጠቃቀም አንፃር በመገምገም የተገኘውን ውጤት ያካተተ ነው።

ከዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ውስጥ ጥሩ የደን ሽፋን ከሚገኝባቸው ጥቂት ቦታዎች ውስጥ አንዱ የሸካ ዞን ነው። የህብረተሰቡ ኑሮም የተመሰረተው በደኑና ከደኑ በሚገኙ ውጤቶች ላይ ነው። በዚህም ምክንያት ህብረተሰቡ የራሱ የሆነ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ የደን አጠባበቅና አጠቃቀም እንዲሁም ደግሞ የባለቤትነት መብት ስርዓት አለው። የዚህ ዓይነቱ ባህላዊ የደን አያያዝና አጠቃቀም ደኑ ለረዥም ዘመናት ተጠብቆ እንዲቆይና ከሌሎቹ የአገራችን አካባቢዎች ጋር ሲነፃፀር በዚህ አካባቢ ያለው ደን ክፉኛ ሳይጎዳ እንዲቆይ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይታመናል። ይህ እንዳለ ሆኖ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን በአካባቢው ግብርናና እና የቡናና ሻይ ተክል ልማት መስፋፋት ጋር ተዳምሮ ከፍተኛ የደን ውድመት በመድረስ ላይ ይገኛል። በተለይም ደግሞ እ.ኤ.አ በ1973, 1987, 2001, እና 2005 የመሬት ሽፋን ለውጥን አስመልክቶ የተወሰደ የሳተላይት ምስል እንደሚያሳየው ከሆነ በየዓመቱ የሚደረገው የደን ምንጠራ (ጭፍጨፋ) መጠን እ.ኤ.አ ከ1990ዎቹ ወዲህ እየተባባሰ መጥቷል። ለዚህ ዓይነቱ የደን ጭፍጨፋ እየተባባሰ መምጣት ዋነኛ ምክንያቶች መካከል ደን ለበስ መሬቶችን ያለበቂ ጥናትና ተገቢ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ለሌላ ኢንቨስትመንት መፍቀድ፣ የአካባቢው ህብረተሰብ የደን አጠባበቅ ባህል መሸርሸር፣ የእርሻ መሬት መስፋፋት እና በመንግስት የሚወጡ ፖሊሲዎችና ህጎች ከጊዜ ወደ ጊዜ መቀያየር/መለዋወጥ ተጠቃሽ ናቸው።

በቅርቡ እንኳን በዚሁ አካባቢ ከ40 በላይ ለሚሆኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለቡናና ሻይ ተክል ልማት ፈቃድ ተሰጥቷል። ከእነዚህ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መካከል በአንደራቻ ወረዳ የሚገኘው የገማድሮ ቡና ተክል ልማት 2,295 ሄክታር መሬት የተሰጠው ሲሆን ተጨማሪ 2,000 ሄክታር መሬት ቃል ተገብቶለታል። ከዚህ በተጨማሪም ኢስት አፍሪካ አግሪ ቢዝነስ የተባለው ድርጅትም በዚሁ ወረዳ ወደ 3,435 ሄክታር የሚጠጋ የደን መሬት ለሻይ ተክል ልማት አግኝቷል። የህብረተሰቡ የባህል ለውጥ በአብዛኛው ሊታይ የቻለው የፕሮቴስታንት እምነት በአካባቢው ከመስፋፋትና የከተማ ነዋሪው ቁጥር ከመጨመር ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይታመናል። የቡናና የሻይ

ተክል ልማቱ በሚፈጥረው የስራ ዕድል ምክንያት ከሌላ አካባቢ ፈልሰው የሚመጡ ሰዎች ቁጥር መጨመርም ለባህል ለውጡ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የእምነት ለውጡ የአካባቢው ህብረተሰብ ለባህላዊ ደን፣ ቅዱስ ስፍራዎችና በቀላሉ ሊጎዱ ለሚችሉ እንደ ወንዞችና ውሃ አዘል የሆኑ የተፈጥሮ አካባቢዎች ያለው አመለካከት እንዲቀየር አድርጓል፡፡ ከህዝብ ቁጥር ማሻቀብ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የማገዶ እንጨት ገበያ መድራቱም የተወሰኑ የአካባቢው ህብረተሰብ አባላት ከማገዶ ሽያጭ በሚገኝ ገቢ እንዲተዳደሩ አድርጓቸዋል፡፡

በመንግስት የሚወጡ ፖሊሲዎችና ህጎችም ቢሆኑ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን የመሬት ባለቤትነት መብትንና አጠቃቀምን እንዲሁም ደግሞ ባህላዊ ደኖቹ ከህብረተሰቡ እምነት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በቅጡ ያገናዘቡ አይመስልም፡፡ በሕገ መንግስቱ በግልፅ የተቀመጠው የህብረተሰቡ የመሬት ባለቤትነት መብት በፌደራል ደረጃም ሆነ በክልል በሚወጡ ፖሊሲዎች የተካተተበት ሁኔታ በግልፅ አይታይም፡፡ ለምሳሌ ሕገ መንግስቱ የመሬት ባለቤት ህብረተሰቡ መሆኑን በግልጽ የሚያስቀምጥ ቢሆንም የፌዴራሉ የመሬት አዋጅም ቢሆን የክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ህጎች ይህን በሕገ መንግስቱ ለህብረተሰቡ የተሰጠውን የባለቤትነት መብት ነጥቀውታል ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ አሁን በስራ ላይ ያለውን ሕገ መንግስት ስንመለከት መሬት የመንግስትና የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሃብት መሆኑ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ ሆኖም በተለያዩ ጊዜያት የወጡ ፖሊሲዎችና ህጎች እርስ በርሳቸው ያለመናበብ ሁኔታዎች ይታይባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ፣ የኢንቨስትመንትና የወንጀለኛ መቅጫ ህጎች እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱበት ሁኔታ በግልፅ ይታያል፡፡ በየደረጃው የሚገኘው የተቋማት አወቃቀርም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ፖሊሲዎችና ህጎችን ለማስፈጸም ያለው አቅም አናሳ ነው፡፡ በመሆኑም የደን ሃብታችንን ዘለቄታነት ባለው መንገድ መጠቀምና የአካባቢ መራቆትን መከላከል የሚቻልበትን መንገድ በዚህ ጥናት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

አግባብነት ያለው የደን አያያዝና አጠባበቅ እንዲኖር ካስፈለገ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከደኑ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድም የሸካ ደንን አስመልክቶ ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን የተለያዩ ግልጋሎቶችና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን ለመዳሰስና መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ለመጠቆም ጥረት ተደርጓል፡፡ ይህ ጥናት በአብዛኛው የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ለማግኘት የተጠቀመበት ዘዴ ከተወሰኑ የህብረተሰብ አካላት ጋር በተደረገ ውይይት፣ ቁልፍ የመረጃ ምንጮችን በቅርበት በማጥናትና ለተወሰኑ ቤተሰቦች መጠይቅ በማቅረብ ነው፡፡ ከዚህ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ በተጨማሪ የሚመለከታቸው የዞንና የወረዳ መስሪያ ቤቶችና ቀደም ብለው በአካባቢው ደን ላይ የተደረጉ ጥናቶችንም ለመጠቀም ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ለናሙና ከተወሰዱ ቤተሰቦች መካከል 44 በመቶ ያህሉ ዋነኛ የገቢ ምንጫቸው ደንና የደን ውጤቶችን በመሸጥ የሚያገኙት ገንዘብ ነው፡፡ ከተፈጥሮ ደኑ የሚገኘው ቀጥተኛ ጥቅም ለቤት ግንባታ፣ ለቤት ውስጥ ቁሳቁስ መስሪያ፣ ለእርሻ መሳሪያዎች እና ለአጥር ግንባታ ሲሆን ይህም በገንዘብ ሲተመን ከአንድ ሄክታር መሬት በአማካይ በዓመት የሚገኘው ገቢ መጠን እስከ ብር 89 ሊደርስ እንደሚችል ተገምቷል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ምንም የደን አስተዳደር በሌለበት ሁኔታ ከደኑ የሚገኘው ጣውላ ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በአንድ ሄክታር በአማካይ ከብር 1,192 እስከ 8,142 እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ምንም ዓይነት የደን አስተዳደር ሳይኖር የህብረተሰቡን ባህላዊ የደን አያያዝና አጠቃቀም ዘዴ ብቻ በመከተል ከሸካ ደን ሊገኝ የሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከአንድ ሄክታር በዓመት እስከ ብር 10,572 እንደሚደርስ ታውቋል፡፡ በዚህ መሰረት ወደ 67,794 ሄክታር የሚደርሰውን ጥቅጥቅ ደንና ወደ 35,077 ሄክታር የሚጠጋውን ዘርዛራ ደን ብንወስድ በዓመት እስከ ብር 1,087 ቢሊዮን የሚደርስ ገቢ ሊገኝ ይችላል ማለት ነው፡፡ የቀርከሃ ደንን ብቻ እንኳን ብንወስድ በተገቢው መንገድ መንከባከብና መጠቀም ከተቻለ በየዓመቱ ከብር 542 እስከ 812 ሚሊዮን የሚደርስ ገቢ ሊያስገኝ እንደሚችል ተገምቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የዚህ የሸካ ደን ካርቦን አከማችቶ የመያዝ አቅሙ እስከ ብር ሁለት ቢሊዮን የሚገመት ሲሆን ይህን የተፈጥሮ ደን ለሰብል ምርት ለመጠቀም የሚያስፈልገው ገንዘብ መጠን ከሚለቀቀው ካርቦን አንጻር ሲታይ በአንድ ሄክታር ከብር 3,400 - 17,425 እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ በአቃላይ ሲታይ ባህላዊ በሆነ መንገድ ጣውላ ነክ ያልሆኑ የደኑን ውጤቶችን በመጠቀም ሊገኝ የሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ መሬቱን ለሻይ ተክል ልማት በማዋል ሊገኝ ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ጋር ሲነፃፀር ሁለት እጥፍ ያህል ልዩነት እንዳለው ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የእነዚህ ጥናቶች ውጤት ረጅም ዕድሜ ያለውን ይህን የሸካ ደንን በአግባቡ በመጠበቅና በመጠቀም እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

## 1. መግቢያ

የመሬት አጠቃቀም ስርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ መለዋወጥ በዓለማችን ላይ የተለመደ ክስተት ነው። ለእነዚህ ለውጦችም በርካታ ምክንያቶች ሲኖሩ መሰረታዊ መንስዔዎቻቸው ግን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ መሰረቶች ያላቸው ናቸው። የተለያየ መንስዔ እንዳላቸው ሁሉ ሊያስከትሉ የሚችሉት ውጤትም የተለያየ ሊሆን ይችላል። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህልም የመሬት ሽፋን መለዋወጥ/መቀያየር ብዝሃ ህይወትን፣ አካባቢን፣ ስነ-ምህዳራዊ አገልግሎትን፣ የአካባቢውን ህብረተሰብ አኗኗር ሁኔታ፣ በመሬቱ ከመጠቀምና ከባለቤትነት መብት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ግጭቶችንና ባህላዊ የእምነት ስርዓትን ሊጎዳ እንደሚችል ይታመናል። እውነታው ይህ ቢሆንም በብዙ ጥናቶች ጎልቶ የሚወጣው ጉዳይ የደን ሽፋን ለውጥ በብዝሃ ህይወት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ወይም ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ጎኑ ብቻ ነው።

በመልካ ማህበር የተደረጉት ዘርፈ ብዙ ጥናቶች ውጤት ከዚህ በተለየ መልኩ የተለያዩ እውነታዎችን የዳሰሰ ነው። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሸካ ዞን ማሻና አንደራቻ ወረዳዎች የተከሰተው የመሬት አጠቃቀም ለውጥ በደኑ ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል። ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው የሸካ ዞን በአገራችን ከፍተኛ የደን ሽፋን ከሚገኝባው አካባቢዎች አንዱ ነው። በአሁኑ ወቅት ግን ከኢንቨስትመንት እና ከእርሻ መስፋፋት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የሆነ የደን ውድመት እየደረሰበት ያለ አካባቢ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህ ጥናት መነሻ ምክንያት የሆነውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየደረሰ ያለው የደን ሽፋን ለውጥ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱ ነው። በዚህ ጥናት የመሬት ሽፋን ለውጡን በተመለከተ ያለውን ሁኔታ ከሚከተሉት አምስት የተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር ለመቃኘት ጥረት ተደርጓል። እነርሱም፡-

1. በተለያዩ ዓመታት በተወሰዱ የሳተላይት ምስሎች ከሁለቱ ወረዳዎች በተመረጡ ቀበሌዎች ውስጥ የታየውን የመሬት አጠቃቀም ለይቶ ማውጣት፤

2. የመሬት አጠቃቀም መለዋወጥ በብዝሃ ህይወት ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ፤
3. የባህል ለውጥ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው የደን አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚያሳድረው ጫና፤
4. ደንና የደን ውጤቶችን በዘለቄታነት ለመጠቀም የሚያስችል ህጋዊና ተቋማዊ አደረጃጀት ትንተና እና፤
5. የተፈጥሮአዊ ደን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚሉት ናቸው፡፡

## 2. የጥናቱ መነሻ

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት እንደ አገራችን የአየር ጸባይ ከሆነ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አብዛኛዎቹ ቦታዎች በደን መሸፈን ነበረባቸው፡፡ ሆኖም ግን ላለፉት ሁለትና ሶስት ክፍለ ዘመናት ያህል እየጨመረ ከመጣው የህዝብ ብዛትና ሰፈራ ጋር ተያይዞ የአካባቢው ደን ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሽቆልቆል ላይ ይገኛል፡፡ አልፎ አልፎ ከሰሜኑ ወደ መካከለኛውና ደቡብ የአገሪቱ ክፍል የሚደረገው የህዝብ ፍልሰትም ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲካሄድ እንደነበረ አንዳንድ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ የዚህ ዓይነቱ ፍልሰት በአጼ ምኒሊክ የመስፋፋት ዘመን ከፍተኛ እንደነበርና በንጉስ ኃይለ ስላሴ ዘመንም እንደቀጠለ ይታወቃል፡፡

ከሌላው የአገሪቱ ክፍል ጋር ሲነፃፀር በደቡብ ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች የነበረው የደን ሽፋን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከፍተኛ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ባለፉት 30 ዓመታት ውስጥ የታየው የደን ውድመት በአገሪቱ ከተከሰተው ሰው ሰራሽ አደጋ ሁሉ የከፋ ነው፡፡ ሪዩሲንግ የተባለ ተመራማሪ እ.ኤ.አ በ1998 እንዳስታወቀው ከሆነ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የደን ሽፋን እ.ኤ.አ 1971-1975 በነበረው ጊዜ አርባ በመቶ የነበረው እ.ኤ.አ በ1997 በግምት ወደ አስራ ስምንት በመቶ አሽቆልቁሏል፡፡ ጥቅጥቅ ያለ ደን ለበስ የሆነ ስፍራን ለሌላ ተግባር ማዋሉ ለደን ውድመት ዋነኛ መንስዔ እንደሆነም ይታወቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ተመራማሪ እንደገለፀው ወደ 235,400 ሄክታር የሚጠጋ ጥቅጥቅና ዘርዛራ ደን እ.ኤ.አ ከ1971-1997 ድረስ በነበረው

ጊዜ ወድሟል። ይህ ማለት በአማካይ በየዓመቱ ወደ 10,000 ሄክታር የሚጠጋ ደን ወድሟል ማለት ነው። የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት የሆነው የሸካ ዞን ከፍተኛ የደን ሽፋን ማለትም ከጠቅላላ የቆዳ ስፋቱ 47 በመቶ ያህሉ በደን የተሸፈነ አካባቢ ነው። ብዙ ዓይነት የቅመማ ቅመም ዓይነቶችና የተለያዩ ስሮቻቸው ተቆፍሮ ለምግብነት የሚውሉ በርካታ ዕፅዋት የሚገኙበት አካባቢ ነው። የማሻና አንደራቻ ወረዳዎች የደቡብ ምዕራብ ከፍተኛ ቦታዎች አካል ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ወረዳዎች ለጥናቱ የተመረጡበት ዋና ምክንያትም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ የሆነ የደን ወድመት የሚታይባቸው አካባቢዎች በመሆናቸው ነው።

እነዚህ አካባቢዎች ከፍተኛ መጠን ላለው የደን ሽፋን ለውጥ ሊዳረጉ ከቻሉባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል የአነስተኛ ገበሬዎች የእርሻ መሬት መስፋፋትን ጨምሮ ቀደም ሲል ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከፍተኛ መጠን ያለው የቡና እና ሻይ ተክል ልማት ኢንቨስትመንት እየተካሄደ ያለበት አካባቢ መሆኑ ነው። እስከ አሁን ድረስ ሰፋፊ የደን መሬትን ለተለያየ ኢንቨስትመንት የመስጠቱ ተግባር እንደቀጠለ ሲሆን ይህም የሚከናወነው ያለ በቂ ጥናትና ተገቢ የሆነ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሳይደረግ እንዲሁም በአካባቢው ህብረተሰብ የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳትም በአግባቡ ሳይጤን ነው።

በሸካ ዞን የኢንቨስትመንት ፈቃድና መሬት ለማግኘት ያለው አሰራር አስቸጋሪ አይደለም። ፈቃዱን ለማግኘት ሁለት የተለያዩ አማራጮች አሉ። አንደኛው አማራጭ የኢንቨስትመንት ቢሮው ጥናት እያደረገ የማስተዋወቅ ስራ የሚሰራበት ሲሆን ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ኢንቨስተሩ ጥናቱን በራሱ አካሂዶ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅበት መንገድ ነው። በአሁኑ ሰዓት በዞኑ ወደ 43 የሚጠጉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ አግኝተው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ስድስት ተጨማሪ ፕሮጀክቶች ደግሞ ስራ ለመጀመር በዝግጅት ላይ ናቸው። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል ወደ 14 ለሚጠጉት ለእያንዳንዳቸው ከ50 ሄክታር በላይ የሚሆን ሰፋፊ መሬት ለቡና እርሻ ልማት ተሰጥቷል።

ሠንጠረዥ 1፡- በቅርቡ በሸካ ዞን ለኢንቨስትመንት የተሰጡ ዋና ዋና ደን ለበስ ስፍራዎች

| ተ.ቁ | የኢንቨስትመት ኩባንያው ስም | ቦታ (በሄክታር) | ወረዳ | ቀበሌ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዛጌ አንበሎ | 80 | አንደራቻ | ዮኪጨጨ | እየተተገበረ ያለ |
| 2 | አበበ አንተነህ እና በላይ ወላሼ | 1500 | አንደራቻ | ዮኪጨጨ | በሂደት ላይ ያለ |
| 3 | ሺሺ ኦፒ | 120 | የኪ | ዳፒ | በሂደት ላይ ያለ |
| 4 | ወርቁ አዶ | 170 | አንዳራቻ | እጨ | ተግባራዊ ያልሆነ |
| 5 | አወል ሙዘይን | 160 | የኪ | አላሙ | ተግባራዊ ያልሆነ |
| 6 | ደንቢ ፏፏቴ | 240 | የኪ | አጫኔ | ተግባራዊ የሆነ |
| 7 | ጋሂበሪ | 85 | የኪ | አጫኔ | ተግባራዊ የሆነ |
| 8 | ተስፋዬ ኢብሮ | 120 | የኪ | ዳዩ | ተግባራዊ የሆነ |
| 9 | የቦራ አግሪ ደቨሎፕመንት | 109 | የኪ | ሺመርጋ | ተግባራዊ የሆነ |
| 10 | ኢስትአፍሪካን ቲ ፕላንቴሽን | 3,435 | ማሻ | ጨዋቃ | ተግባራዊ የሆነ |
| 11 | ገማድሮ ኮፊ ፕላንቴሽን | 2,295 | አንደራቻ | ገማድሮ | ተግባራዊ የሆነ |
| 12 | ገማድሮ ኮፊ ፕላንቴሽን11 | 1,000-2,000 | አንደራቻ | ዱዊና | በሂደት ላይ ያለ |
| 13 | ኮዶ ኮፊ | 70 | ማሻ | ኡሞ | ተግባራዊ የሆነ |
| 14 | ሼቤና ኮፊ | 67 | አንደራቻ | ሼበና | ተግባራዊ የሆነ |

**ምንጭ፡- የሸካ ዞን ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት**

በገማድሮና ዮኪጪጪ ቀበሌዎች ለበርካታ አርሶ አደሮች ለቡና ተክል እንዲጠቀሙበት በማለት ሰፋፊ የደን መሬት ተሰጥቷቸዋል፡፡ የደን መሬትን በቋሚነት ለቡና ተክል መጠቀም ማለት ያንን ደን መልሰን የምናገኝበት መንገድ የለም ማለት ነው፡፡ ያለ በቂ ጥናት የሚከናወን የዚህ ዓይነቱ አካሄድ በአካባቢና በብዝሃ ህይወት ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት በተጨማሪ በደን ሃብት ምክንያት የሚነሱ ግጭቶች እንዲባባሱና ባህላዊው የመሬት ባለቤትነት ስርዓት እንዲጣስና የደን ሃብት አያያዝና አጠቃቀም ዘዴም እንዳይተገበር ያደርጋል፡፡

## 3. የጥናቱ ስፋት/ጥልቀት

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሸካ ዞን በሚገኙት በማሻ እና በአንደራቻ ወረዳዎች በሚገኙ በተመረጡ ደኖች ላይ በእርሻ መስፋፋት፣ በኢንቨስትመንት፣ በሰፈራና በመሰል እንቅስቃሴዎች ሳቢያ የታየውን ለውጥ እና ለውጡን ተከትሎ በብዝሃ ህይወት ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠን ለማወቅ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የጥናቱ ዋነኛ ዓላማዎች፡-

- ☞ ከሁለቱ ወረዳዎች ለጥናቱ የተመረጡት የደን ስፍራዎች በሰው ጣልቃ ገብ እንቅስቃሴ ከመጎዳታቸው በፊት የነበሩበትን ይዞታና መጠን ለማወቅ የሚረዱ የፅሁፍ መረጃዎችንና ከአየር ላይ የተነሱ ፎቶግራፎችንና ከሳተላይት የተወሰዱ ምስሎችን መሰብሰብና ትንታኔ መስጠት፤
- ☞ ቀደም ሲል ደኖቹ በፊት የነበራቸውን የዕፅዋት ዝርያ ዓይነት ለማወቅ የሚረዱ የተለያዩ የህትመት ውጤቶችን መሰብሰብና መተንተን፤
- ☞ በቅርቡ ማለትም እ.ኤ.አ በ2005 የተወሰዱ የሳተላይት ምስሎችን ተጠቅሞ በአሁኑ ሰዓት ደኖቹ የሚገኙበትን ይዞታ ማመላከት፤
- ☞ በደረሰባቸው መነካካት ምክንያት ደኖቹ ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠን አንጥሮ ማውጣት፤
- ☞ በደኖች ላይ በደረሰው ለውጥ ምክንያት በዱር እንስሳትና ዕፅዋት በአጠቃላይ በብዝሃ ሕይወቱ ላይ የደረሰውን ጉዳት መተንተን፤

- ለደን ሽፋኑ መቀያየር ዋነኛ ምክንያቶች ለይቶ ማውጣት እና፤
- ለወደፊቱ ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከልና ብሎም ከደረሰው ጉዳት ደኖቹ ሊያገግሙና ወደ ቀድሞ ይዞታቸው ሊመለሱ የሚችሉበትን ስትራቴጂዎች ለመጠቆም የሚሉት ናቸው።

## 4. ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ እና የአጠናን ዘዴ

### 4.1. ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ/ክልል

ይህ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልል ሸካ ዞን ውስጥ ነው። የዞኑን መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ስንመለከት በሰሜናዊ ኬክሮስ $7^0$ 24'-$7^0$ 52' እና በምስራቃዊ ኬንትሮስ $35^0$ 13' - $35^0$ 35' መካከል ይገኛል። በዞኑ ማሻ፣ አንዳራቻ እና የኪ የተባሉ ሶስት ወረዳዎች ይገኛሉ። በሶስቱም ወረዳዎች የሚገኙት ቀበሌዎች ቁጥር 63 ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 56 ያህል የገጠር ቀበሌዎች ናቸው። የዞኑ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 2175.25 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ሲሆን በግምት ወደ 47 በመቶ ያህሉ የቀርከሃ ተክልን ጨምሮ በደን የተሸፈነ ነው።

ዞኑ ከባህር ወለል በላይ የሚገኝበት ከፍታ ከ900-2700 ሜትር የሚደርስ ሲሆን በዓመት በአማካይ ከ1800-2200 ሚሊ ሜትር የሚደርስ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያገኛል። ጥናቱ ያተኮረው በዞኑ በሚገኙ ሁለት (አንደራቻና ማሻ) ወረዳዎች ላይ ሲሆን የባህላዊ ለውጥ ጥናቱ ግን የተካሄደው ከማሻ ቀበሌ በተመረጡ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ብቻ ነው።




ስዕል 1.1 የጥናት ቦታውን የሚያሳይ ካርታ

### 4.2. የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ በባህሪው ብዙ ዘርፎችን ያካተተ ነው፡፡ በጥናት ክፍል ሁለት የመሬት ሽፋን ለውጥን ለማግኘት በተደረገው ጥናት በተለያዩ አራት ጊዜያት ማለትም እ.ኤ.አ ጥር 1973፣ የካቲት 1987፣ የካቲት 2001 እና መጋቢት 2005 የተወሰዱ የሳተላይት ምስሎችን እርስ በእርሳቸው በማነፃፀር ያለው ለውጥ ተጠንቷል፡፡ በክፍል ሶስት የደኖቹን ብዝሃ ህይወት ሃብት መጠን ለመዳሰስ በተደረገው ጥናት ዋና ዋና በሆኑ የደን ዕፅዋት ዓይነት ላይ ፈጣን

የብዝሃ ህይወት የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በቂ መረጃ ሊሰጡ ከሚችሉ ግለሰቦች ጋር በመሆን በተመረጡ ናሙና ቦታዎች ላይ በመዘዋወር የተለያዩ የዕፅዋት ዝርያዎች ተመዝግበዋል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የዕፅዋቶችን ተፈጥሮአዊ ባህሪና የአካባቢው ህብረተሰብ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚጠቀምባቸውን ዝርያዎች ለመለየት ተሞክሯል፡፡ እነዚህን ዝርያዎች ለይቶ ለማወቅ የሚረዳና መረጃ ለመሰብሰብም ስርዓት ያለው የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ስራ ላይ ውሏል፡፡

በክፍል አራት የባህላዊ ለውጥን ለማጥናት በተደረገው ጥናት በቂና አስተማማኝ ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ የተለያዩ የጥናት ዘዴዎች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ከእነዚህ የጥናት ዘዴዎች መካከል የተሳታፊዎች ምልከታ፣ የቡድን ውይይትና ዘርዘር ያለ ቃለ መጠይቅ ይገኙበታል፡፡ ይህ ጥናት ያተኮረው በቶና እና ምሎ ሽባ በሚባሉ ማሻ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች ላይ ነው፡፡ የባህል ለውጥ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም ላይ የሚኖረውን ተፅእኖ ለማጥናት እነዚህ ሁለት ቀበሌዎች የሻይ ልማት ከሚካሄድበት ተዋሳኝ ቀበሌዎች በመሆናቸው በቂ መረጃ ለማግኘት ወካይ ቦታዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የህግና ተቋማዊ ትንታኔዎችንም በተመለከተ በክልል መንግስታት፣ በፌደራል መንግስትና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሚገኙ የህግና የፖሊስ ማዕቀፎችን እንዲሁም ደግሞ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ህግ አስፈፃሚ ተቋማትንና የአሰራር ዘዴዎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ የጥናት ቡድኑ በዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች፣ በአገሪቱ ህገ መንግስት፣ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምንና የህብረተሰቡን መብት አስመልክቶ በወጡ ፖሊሲዎችና አዋጆች፣ የክልል መንግስታት ያወጧቸው ፖሊሲዎችና አዋጆች እና እነዚህን ፖሊሲዎችና አዋጆች ለማስፈፀም የተዘረጉ ተቋማት መካከል ያለውን ቁርኝት በጥልቀት ተመልክቶታል፡፡

የኢኮኖሚ ጠቀሜታውን ለመገመት በተደረገው ጥናት የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ መሰብሰብ፣ የቡድን ውይይትና በቂ መረጃ ሊሰጡ

ከሚችሉ ግለሰቦች እና ቤተሰቦች ጋር ውይይት ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዞንና በወረዳ ደረጃ ከሚገኙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት ባለስልጣናትና ቀደም ሲል በአካባቢው ላይ ተደርገው ከነበሩ ጥናቶች ቀጥተኛ ያልሆኑ መረጃዎችን ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡

## 5. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

### 5.1. የመሬት ሽፋን/ገፅታ ለውጥን በተመለከተ

የሁሉም ወረዳዎች የመሬት ሽፋን/ገጽታ ለውጥ የተጠናው እ.ኤ.አ በ1973፣ 1987 እና 2001 ተወስደው ከነበሩት የሳተላይት ምስሎች ነው፡፡ በዚህም መሰረት በሁሉም ቦታዎች ላይ በደን ተሸፍኖ የነበረው መሬት መጠን እየቀነሰ እንደመጣ ተመልክቷል፡፡ ለምሳሌ ያህል እ.ኤ.አ በ1987 ጥቅጥቅ ያለ ደን መጠን ወደ 55,304 ሄክታር ይጠጋ የነበረው እ.ኤ.አ በ2001 ወደ 43,424 ያህል የነበረው አሽቆልቁሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከላይ በተጠቀሰው ተመሳሳይ ወቅት ወደ 46,594 ሄክታር ያህል የነበረው ዘርዛራ መጠን ወደ 35,077 ሄክታር ሊወርድ ችሏል፡፡ በሌላ በኩል በዚሁ ተመሳሳይ ወቅት የተጎዳ ደን መጠን 8,015 ሄክታር ወደ 24,370 ሄክታር ሲያሻቅብ ለእርሻ የዋለው መሬት መጠንም ከ8,620 ሄክታር ወደ 14,672 ሄክታር ከፍ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ ውጤት መረዳት እንደሚቻለውም ለመሬት ሽፋኑ ለውጥ ዋነኛ መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉት የሰው ጣልቃ ገብ እንቅስቃሴ እና የእርሻ መሬት መስፋፋት ናቸው፡፡ በ14 ዓመታት ውስጥ ብቻ ለሰብል እርሻ የዋለው መሬት መጠን በእጥፍ ለማደግ መቻሉን አንዳንድ መረጃዎች ሲያሳዩ በቀርከሃ በተሸፈነ መሬትና እርጥበት አዘል በሆኑ ቦታዎች ሰፊ የደን መሬት የመጠቀሙ ጉዳይ በአካባቢው የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል እ.ኤ.አ በ2001 በዞኑ በሻይ ተክል የተሸፈነው መሬት መጠን 758 ሄክታር የነበረ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ1987 በሻይ ተክል የተሸፈነ መሬት ጨርሶ እንዳልነበረ አንዳንድ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የቡናና ሻይ ተክል ልማትን ጨምሮ ለደን ሽፋን መሳሳት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎች ሁሉ የሚገኙባቸው ስለሆኑና በአብነት ሊቀርብ ስለሚችሉ ጠለቅ ያለ ጥናት የተካሄደው በተመረጡ ሁለት ቦታዎች ላይ ነው። ከሁለቱ ቦታዎች አንደኛው ከኢስት አፍሪካ ሻይ ልማት ጋር የሚዋሰን ሆኖ አራት የተለያዩ ቀበሌዎችን ማለትም ኡዋ፣ ቂጃ ጨዋቃ፣ ዎሎና በቶ ቀበሌዎችን ያካተተ ነው። በእነዚህ ቀበሌዎች የታየው የዳሰሳ ሽፋን ለውጥ ዓይነት አጭር መግለጫ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 2፡- የደን ሽፋን ለውጡ አጠቃላይ ገጽታ

| የደን ሽፋን በመቶኛ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **የደን ሽፋኑ ዓይነት/ ዓመት** | **1973** | **1987** | **2001** | **2005** |
| ጥቅጥቅ ያለ ደን (ዱና ድንባሮ) | 60 | 50 | 32 | 20 |
| ዘርዛራ ደን (ቃጫሞ) | 0 | 9 | 28 | 30 |
| ልቅ ደን (ዳሾ) | 26 | 25 | 18 | 21 |
| የዘር ሽፋን ያለው ታራሽ መሬት (ጉዮ ጣኦ) | 2 | 2 | 2 | 2 |
| ለተለያየ ግብርና የዋለ (ቂጂ ጉዎ) | 5 | 7 | 9 | 10 |
| የታረሰ መሬት | 5 | 3 | 3 | 6 |
| ውሃ አዘል መሬት (ጨጮ) | 3 | 3 | 3 | 3 |
| ቡናና ሻይ እርሻ ልማት | 0 | 0 | 5 | 8 |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ጥቅጥቅ ያለ ደን ሽፋን መጠን እ.ኤ.አ በ1973 ስድሳ በመቶ የነበረው እ.ኤ.አ በ2005 ወደ ሃያ በመቶ ገደማ አሽቆልቁሏል። በሌላ በኩል ግን ዘርዛራ ደን መጠን ዜሮ በመቶ የነበረው ወደ ሰላሳ በመቶ፣ የግብርና መሬት ከአምስት በመቶ ወደ አስር በመቶ እና የቡና እና ሻይ እርሻ ልማት ሽፋን

ከዜሮ በመቶ ወደ ስምንት በመቶ ከፍ ለማለት ችሏል። በአጠቃላይ ሲታይ የተፈጥሮ ደንን ለግብርናና እርሻ ልማት ማዋልና የሰው ጣልቃ ገብነት በአራቱ ቀበሌዎች ለተከሰተው ለመሬት ሽፋን መለዋወጥ ዋነኛ ምክንያት በጨዋቃ-ኡቶ የተቋቋመው የሻይ ተክል ዋነኛው እንደሆነ ይታወቃል።

የኢስት አፍሪካ ሻይ ተክል ልማት የተባለው ኩባንያ ሁለት የተለያዩ የይዞታ ካርታ አዘጋጅቶ አሰራጭቷል። ይህ ኩባንያ ከአንደኛው የይዞታ ካርታው ውጭ የሚገኝ ወደ 266 ሄክታር የሚጠጋ እንዲሁም ደግሞ ከሁለተኛው የይዞታ ካርታ ውጭ የሚገኝ ወደ 196 ሄክታር የሚጠጋ መሬት ላይ የነበረን ደን አስመንጥሯል። ከዚህ በተጨማሪም ከባሮ ወንዝ ጋር በሚዋሰነው ይዞታው ቢያንስ 1200 ሜትር ስፋት ያለው የደን ቦታ ከልሎ ለመንከባከብ የገባውን ቃል አፍርሶ በአሁኑ ሰዓት ከባሮ ወንዝ ዳርቻ ያለው ርቀት በ2005 የሳተላይት ምስል መረጃ መሰረት 90 ሜትር ብቻ ነው።

በገማድሮ የቡና ተክል ልማት ያለው የደን ሽፋን ለውጥ ደግሞ ከዚህ የባሰ ነው። ለምሳሌ ያህል እ.ኤ.አ በ1973 ጥቅጥቅ ያለው ደን መጠን ከገማድሮ ቀበሌ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት ውስጥ 78 በመቶ ያህሉን ይሸፍን ነበር። የዚህ ሽፋን መጠን እ.ኤ.አ በ2005 ወደ አስራ ስድስት በመቶ ዝቅ ብሏል። የቡና ልማትን በሚመለከት ግን እ.ኤ.አ ከ1973 እስከ 2005 ድረስ በነበሩበት ዓመታት ከባዶ ተነስቶ በሰላሳ ሶስት በመቶ ያህል ሊያድግ ችሏል። በተመሳሳይ መልኩ ሰፋፊ የደን ቦታዎችን የመመንጠርና ለእርሻ የመጠቀም ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቷል። ከፍተኛ የሆነ የደን ውድመት የደረሰው በገማድሮ ሲሆን ወደ አስራ ሁለት ነጥብ ሁለት በመቶ የሚደርስ ደን በየዓመቱ በመውደም ላይ እንደሚገኝ ታውቋል። የገማድሮ ቡና ልማት ፕሮጀክት በአካባቢው መጀመሩን ተከትሎ አርሶ አደሮችና ሌሎች አነስተኛ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በቡና ልማት ላይ በመሰማራታቸው የአካባቢውን ደን ውድመት አባብሶታል።

ሠንጠረዥ 3፡ በገማድሮ የቡና ተክል ልማት አካባቢ በተለያዩ ዓመታት የታየው የመሬት ሽፋን ለውጥ

| የደን ሽፋን በመቶኛ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የደን ሽፋኑ ዓይነት/ዓመት | 1973 | 1987 | 2001 | 2005 |
| ጥቅጥቅ ያለ ደን | 78 | 43 | 15 | 16 |
| ዘርዘር ያለ ደን | 7 | 8 | 17 | 17 |
| ልቅ ደን | 14 | 43 | 42 | 12 |
| የዘር ሽፋን ያለው ታራሽ መሬት | 1 | 5 | 6 | 33 |
| ለተለያየ ግብርና ስራ የዋለ | 0 | 0 | 18 | 14 |
| የታረሰ ወይም ገላጣ መሬት | 0 | 0 | 2 | 1 |
| ሳተላይት ምስሉ ላይ በተፈጠረው የደመና ሽፋን ምክንያት መለየት ያልተቻለ | | | 2 | 1 |

## 5.2. ብዝሐ ሕይወትና የመሬት ሽፋን መለዋወጥ

በዚህ ጥናት እንደታየው ከሆነ በማሻና አንደራቻ ወረዳዎች የሚገኘው ደን በርካታ የዕፅዋት ዝርያዎች የሚገኙበት ነው፡፡ በማሻ ወረዳ የሻይ ልማቱ አዋሳኝ በሆኑት በኡቶ፣ በሳቶ፣ በጋቲራና ጨዋቃ ደኖች ብቻ ወደ 190 የሚደርሱ የዕፅዋት ዝርያዎችን ለመመዝገብ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የገማድሮ ቡና ልማት አዋሳኝ ከሆነው ከገማድሮ ደን ወደ 180 ዝርያዎች ተመዝገበዋል፡፡ በማሻ እና አንደራቻ ወረዳ ለናሙና ጥናት በተከለሉ አምስት ቦታዎች ላይ በተደረገ ጥናት በትናንሽ ቦታዎች ውስጥ የተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች አማካይ ቁጥር በማሻ 32 በአንደራቻ ደግሞ 27 ነው፡፡ እነዚህ የጥናት ቦታዎች እንደ ጥቁር እንጨት (Prunus africanus) ለመሰሉ አደጋ ላይ ላሉ እና እንደ ሲሲኖ (Canarina

abyssinica) ለመሳሰሉ ብርቅዬና ጥቂት ለሆኑ ዝርያዎች ጠቃሚ እንደሆነም ታውቋል፡፡

የአካባቢው ህብረተሰብም በደኑ ውስጥ የሚገኙትን ዕፅዋቶች ለተለያየ አገልግሎት ይጠቀምባቸዋል፡፡ ከተመዘገቡት ዕፅዋቶች መካከል አብዛኞቹ አንድና ከዚያ በላይ ጥቅም የሚሰጡ ናቸው፡፡ በሁለቱ ወረዳዎች ከጣውላና አጣና በተጨማሪ ሌሎች የደን ውጤቶች ለምግብነት፣ ለቤት ግንባታ፣ ለእንስሳት መኖነት፣ ለመድሃኒትነትና ለማገዶነት ይውላሉ፡፡ የማር ምርትም ጣውላ ነክ ካልሆኑ የደን ውጤቶች መካከል የሆነ ዋነኛው የገቢ ምንጭ ነው፡፡

ደን ለበስ መሬትን ለሌላ አገልግሎት መጠቀም ለዕፅዋት ዝርያ ዓይነቶች መመናመን ዋነኛ ምክንያት ሆኗል፡፡ በኢስት አፍሪካ የሻይ ልማት ኩባንያ የተመነጠረው የደን መሬት የተተካው በሁለት ዓይነት ተክል ማለትም በሻይ እና በባህር ዛፍ ተክል ብቻ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ከዕፅዋት ዝርያ የዓይነት ብዛት አንፃር ሲታይ ለብዝሃ ህይወቱ ትልቅ ኪሳራ ነው፡፡ መሬቱ ለእርሻ ስራ ውሎ ቢሆን ኖሮ ይህን ያህል አስከፊ ጉዳት አይደርስም፡፡ ምክንያቱም አርሶ አደሩ በተለምዶ ማሳ መሃልና ድንበር አካባቢ ዛፎችን ሳይቆርጥ የማቆየት ልምድ አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለእርሻ በሚውል ተዳፋት አካባቢ ደኑን ተንከባክቦ ማቆየት በብዛት የተለመደ ክስተት ነው፡፡ የሻይ ልማትን ስንመለከት ግን ተዳፋት ቦታ ላይ የሚገኝ ደን ሳይቀር ተመንጥሮ ነው በሻይ ተክሉ እና በባህር ዛፍ የሚተካው፡፡

በአገራችን ሌሎች አካባቢዎች ከሚታየው የቡና ተክል ልማት ጋር ሲነፃፀር የገማድሮ ቡና ተክል በጣም አጥፊና አውዳሚ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ያለውን የቡና አመራረት ብንመለከት በአንድ ሄክታር መሬት ላይ በአማካይ ወደ 300 የሚደርሱ የተለያዩ ዛፍ ዝርያዎች ለጥላነት ሳይቆረጡ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ በገማድሮ ግን በአንድ ሄክታር የቡና መሬት ላይ ለጥላ የሚቀረው ዛፍ ቁጥር ከሃያ አይበልጥም፡፡ በአካባቢው ለረዥም ጊዜ የቆዩት ዝርያዎች እየተቆረጡ እንደ ግራንግር

(Sesbania sesban) የመሳሰሉ ለከብቶች መኖነት ተብለው የገቡ መጤ ዝርያዎች በስፋት በመተከል ላይ ይገኛሉ። ይህንን ልቅ የሆነ አጠቃቀም በመመልከት አርሶ አደሮችና አነስተኛ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የተፈጥሮ ደንን መንጥረው መሬቱን ለቡና ልማት በማዋል ላይ ይገኛሉ። የቡና ልማቱ ዋና ዓላማም ከፍተኛ የቡና ምርት ማግኘት እንደ መሆኑ መጠን ብዙ የዛፍ ጥላ የማያስፈልጋቸው የቡና ዝርያዎች የመትከል አዝማሚያ ከመስፋፋቱ የተነሳ ለጥላነት የሚያገለግሉ ዛፎች ቁጥር በእጅጉ እንዲመናመን አድርጓል።

## 5.3. ባህልና የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ

በባህልና በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ዙሪያ የተደረገው ጥናት የተካሄደው ከኢስት አፍሪካ ሻይ ልማት ተዋሳኝ በሆኑ በበቶና ወሎ ሸባ ቀበሌዎች ነው። እነዚህ የህብረሰተብ ክፍሎች ከአካባቢው ጋር ያላቸው ቁርኝት ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ የራሳቸው የሆነ ባህላዊ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና ጥበቃ ዘዴ አላቸው። ለሸካ ህዝብ ደን ማለት ሁሉንም ነገር ማለት ነው። እንደ ማር፣ ቅመማ ቅመምና ለቤት ግንባታ የሚውሉ የደን ውጤቶችን የሚያገኘው በአካባቢው ካለው ደን ነው። እያደነ የሚበላቸው የዱር እንስሳት ሊኖሩ የሚችሉት ደኑ ከተጠበቀ ብቻ መሆኑን ያውቃል። ከዚህ በተጨማሪም ለሸካ ህዝብ ደኑ በባህላዊ እምነቱ የአምልኮ ስርዓት የሚከናንወንበት፣ የቀብር ስርዓት የሚፈፀምበትና ከዚህም አልፎ ለልጅና ለልጅ ልጆች በውርስ የሚተላለፍ ሃብት ነው።

ይህ ጥናት በተደረገበት አካባቢ የሚገኘው ደን ባህላዊ ደን እና ትልቅ የደን መሬት በመባል ለሁለት ይከፈላሉ። የሁለቱ ዓይነት ደኖች አስተዳደርም የተለያየ ነው። ባህላዊ ደኖች በአብዛኛው የሚገኙት ኮረብታማና ተራራማ በሆኑ የገጠር አካባቢዎች ሲሆን የቆቦ ደን ግን በአብዛኛው የሚገኘው ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ባለ ስፍራ ነው። በሁለተኛ ደረጃ የባህላዊ ደኖች አስተዳደር የተመሰረተው በባህላዊ የይዞታ ስርዓት ላይ ሲሆን የቆቦ ደን አስተዳደር ግን የተመሰረተው ደኑን ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው

በወረሱት ግለሰቦች መብትና ግዴታ ላይ ነው። ባህላዊ ደኖች፣ እርጥበት አዘል መሬቶች፣ የወንዝ ዳር ደኖችና የውኃ ፏፏቴዎች ባህላዊ የእምነት ስርዓት የሚካሄድባቸው ቦታዎች በመሆናቸው በህብረተሰቡ የተለየ ጥበቃ ሲደረግላቸው ቆይቷል።

በሸካ ዞን ባህላዊ ደኖች፣ ውሃ አዘል ቦታዎች የወንዞች ዳርቻ ደኖችና የውሃ ፏፏቴዎች የባህላዊ የእምነት ሰርዓቶች የሚካሄዱባቸው ቦታዎች በመሆናቸው የተለየ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያስገድዱ ባህላዊ አሰራሮች አሉ። ለአምልኮ ስርዓት የሚጠቀሙበት ባህላዊ ደን ‹‹ጉዶ›› ሲባል ፀሎት ወይም ሃይማኖታዊ ስርዓት በስሩ የሚካሄድ ትልቅ ዛፍ ደግሞ ‹‹ዴዶ›› በመባል ይታወቃል። በውሃ አዘል ቦታዎች በወንዞችና በደን መካከል ተፈጥሮአዊ ትስስር እንዳለ ሸካዎች ጠንከር ያለ እምነት ያላቸው ሲሆን ውሃ አዘል ቦታዎች ለወንዞችና ደኖች መገኘት ምክንያት መሆናቸውን ይገልፃሉ። ይህም ማለት በወንዞች ዳርቻ የሚገኙ ተፈጥሮአዊ ደኖች፣ ፏፏቴዎችና ውሃ አዘል ቦታዎች ለወንዞቹ ጤናማ ሆኖ መኖር ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

በመሆኑም የሸካዎች የተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅና አጠቃቀም ዘዴ እነዚህን ተፈጥሮአዊ ትስስር በዘላቂነት በመጠበቅ ላይ የተመሰረተ ነው። ማህበራዊ አደረጃጀታቸውም አካባቢንና የተፈጥሮ ሃብትን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የተመቻቸ ነው። የሸኪቾ ህዝቦች የራሳቸው የሆነ ሸኪታቶ ተብሎ ከሚጠራው የማህበረሰቡ መሪ ወይም ንጉስ ጀምሮ እስከ ተራ የህብረተሰቡ አባል የሚደርስ የአስተዳደር ስርዓት አላቸው። በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የአስተዳደር አካላት ተፈጥሮን የመንከባከብ ኃላፊነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ማህበራዊ አደረጃጀት አላቸው። ‹‹ገዲታቶ›› በመባል የሚታወቁት የጎሳ መሪዎችም የአስተዳደርና ባህላዊ የአምልኮ ስርአት የመምራት ኃላፊነት አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪም ከሌላ አካባቢ በመምጣት ለሚቀላቀሏቸው ሰዎች መሬት የመደልደልና ህዝቡን ‹‹የማንፃት›› ስርአት ያካሂዳሉ። የዚህ ዓይነቱ ባህላዊ እምነት ለአካባቢና ለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ በተለይም ውሃ አዘል ቦታዎችንና ደን ከመንከባከብ ረገድ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየታዩ ባሉት የተቋማት የአደረጃጀት ለውጥ ምክንያት፣ የደን ሽፋንና ሃይማኖት/እምነት መለዋወጥ ምክንያት ህብረተሰቡ የደን ሃብትን በመጠበቅና በመንከባከብ ረገድ በነበረው ግንዛቤ ላይ ለውጦች በመታየት ላይ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል የደን አስተዳደር በጎሳ መሪዎች ቁጥጥር ስር ነበር፡፡ እነዚህ የጎሳ መሪዎች ደኑን የማስተዳደርና አለአግባብ ደኑን በሚጨፈጭፉ አባላት ላይም ቅጣት የመጣል መብት ነበራቸው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ እ.ኤ.አ ከ1997 ጀምሮ ባህላዊ ደኖችን ጨምሮ የድንበር ክለላ በማድረግ በባህላዊ ዘዴ በህብረተሰቡ ይተዳደሩ የነበሩት ደኖች ሁሉ በመንግስት ደንነት በመፈረጃቸው የደን ምንጠራው ሊባባስ ችሏል፡፡ በዚህ የደን አከላለል ስርዓት ከዚህ በፊት በማህበረሰቡ ይተዳደሩ የነበሩ ‹‹ኮቦ›› በመባል የሚታወቁ ሰፋፊ የደን ስፍራዎች፣ ‹‹ጉዶ›› ወይም ባህላዊ ደኖች፣ የቀብር ስፍራዎች፣ ውሃ አዘል ስፍራዎችና በባሮ ወንዝ ዳር የሚገኙ ደኖች ለሻይ ተክል ልማት በኢንቨስትመንት ስም ተሰጥቷል፡፡ እነዚህ በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጣቸው የተፈጥሮ ቦታዎች ዓይናቸው እያየ በቡልዶዘር በመታረሱ የእምነታቸውን ስርዓትና የኃላፊነት ስሜታቸውን ሸርሽሮታል፡፡ እነዚህ አርሶ አደሮች ‹‹ቆቦ›› የተባለውን ደናቸውን የተነጠቁት ያለ ምንም የካሳ ክፍያ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ዋነኛ የገቢ ምንጫቸው የሆነው ደናቸውን ካጡ በኂላ የተወሰኑት ወደ አጎራባች የኦሮሚያ አካባቢዎች በመሰደድ በትርፍ የጋራ የንብ ማነብ ስራ ላይ ሲሰማሩ የተቀሩት ደግሞ በሻይ ልማቱ ውስጥ በቀን ሰራተኝነት ተቀጥረው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡

ወደ አካባቢያቸው ከመጣው የሻይ ልማት ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ከሌሎች አካባቢዎች በመምጣት በሻይ ልማቱ ውስጥ ተቀጥረው በመስራት ላይ ያሉ በርካታ ሰዎች ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ አንዳንድ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ተከስተዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል ስርቆትና ግድያ የመሳሰሉት የወንጀል ድርጊቶች እየተለመዱ የመጡ ሲሆን የበሽታ ወረርሽኝ፣ ፍቺ እና የቤተሰብ መበታተን እየጨመረ መጥቷል፡፡ ከዚህም አልፎ ለባህላዊው የኮቦ

አሰራር ትልቅ ፈተና እስከ መሆን የደረሰ የማርና የቀፎ ስርቆት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመባባስ ላይ ይገኛል፡፡

የጎሳ መሪዎቹ ደኑን ለመንከባከብ ያደርጉት የነበረው ጥረትም የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በአካባቢው መስፋፋቱን ተከትሎ እየተዳከመ ሊመጣ ችሏል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለበት ዋና ምክንያት በፕሮቴስታንት ክርስትና እምነት እንደ መሃላ፣ እርግማንና፣ ባህላዊ የአምልኮ ስርዓቶች የመሳሰሉት ተቀባይነት ስለሌላቸው ነው፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ደግሞ በሸካ ህዝብ ዘንድ የተፈጥሮ ሃብትን ለመንከበካብ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የጎላ ተሳትፎ እንደነበራቸው ይነገራል፡፡ በመሆኑም የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በአካባቢው መስፋፋት በባህላዊው የተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅ ላይ ጫና አሳድሯል ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ በባህላዊ አሰራር ለብዙ ዘመናት ተጠብቀው የቆዩት ባህላዊ ደኖች፣ ውሃ አዘል ስፍራዎችና የወንዝ ዳር ዛፎች ለአደጋ እየተጋለጡ ነው፡፡

## 5.4. ሕጋዊና ተቋማዊ ስርዓት

በዚህ የጥናት ርዕስ ስር ዓለም ዓቀፋዊ ስምምነቶችን፣ ፌደራልና ክልላዊ ፖሊሲዎችንና ህጎችን እንዲሁም ደግሞ ተቋማዊ አደረጃጀትንና የህጎችን አተገባበር (በተለይም በሸካ ዞን ላይ) ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የተወሰኑ ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን በተለይም ደግሞ የህብረተሰቡን ችግር ይፈታሉ ተብለው የሚገመቱትን እንዳልፈረመች ይታወቃል፡፡ የሕግ አስገዳጅነት ያላቸውን እ.ኤ.አ በ1957 እና በ1989 በዓለም ዓቀፍ የስራ ድርጅቶች የወጣውን ስምምነትም አልተቀበለችም፡፡ እስከ አሁን ድረስ ባለው ጊዜ እ.ኤ.አ በ1989 የዓለም ዓቀፉን የስራ ድርጅት ቁጥር 169 ስምምነት አንድም የአፍሪካ አገር ተቀብሎ አላፀደቀውም፡፡ በአጠቃላይ የተለያዩ ዓለም ዓቀፋዊ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች፣ የአናሳዎች መብት፣ የህዝብ መብትና አገር በቀል መብት በማለት የጋራ መብት አስቀምጠዋል፡፡

በአገራችንም እ.ኤ.አ በ1995 የተደነገገው ሕገ መንግስት ለብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች እስከ መገንጠል የሚደርስ ሕገ መንግስታዊ መብትን ሰጥቷል (አንቀጽ 39)። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የህዝቦች መብት የሚወሰነውና የሚተገበረው ህዝቦቹ በሚኖሩበት ግዛት ባለው መንግስት መሆኑን ነው። የኢትዮጵያ ሕገ መንግስትም የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦችን የመሬት ባለቤትነት መብት ተቀብሏል። ሆኖም ግን ይህን ሕገ መንግስታዊ የህዝቦችን መብት ወደ ጎን በመተው መንግስት ብቸኛ የመሬት ባለቤት ሆኖ የሚቀርብበት ሁኔታ ይታያል። በዓለም ዓቀፍ የስራ ድርጅት (ILO) እ.ኤ.አ 1989 የወጣው ስምምነት ውስጥ እንደተካተተው አካባቢን ለመጠበቅና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት የሚረዱ በርካታ ደንቦችና መመሪያዎች ከመገኘታቸው በተጨማሪ የአንድ አካባቢ ህብረተሰብ ከመሬቱ ጋር ላለው የቁርኝት መብት እውቅና የሚሰጡ ናቸው።

በዓለም ዓቀፉ የሲቪልና ፖለቲካዊ መብት ሰነድ አንቀፅ 27 እንደተጠቀሰው የተወሰኑ ዓለም ዓቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች የህብረሰተቡን የጋራ መብት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይቀበላል። ብዙዎች ዓለም ዓቀፍ የአካባቢ ሰነዶችም በአካባቢ ጥበቃና በነዋሪው መካከል ያለውን ግንኙነት ይዳስሳሉ። ኢትዮጵያም ከዓለም ዓቀፉ የስራ ድርጅት ስምምነት ቁጥር 169 በስተቀር ከላይ የተጠቀሱትን ስምምነቶች ተቀብላለች። የብዝሃ ህይወት ስምምነትንም እ.ኤ.አ ጁን 10 1922 የፈረመች ሲሆን እ.ኤ.አ አፕሪል 5,1994 አፅድቃዋለች። እ.ኤ.አ በ1995 በተደነገገው ህገ መንግስት አንቀጽ 9 ላይ እንደተቀመጠው ደግሞ አገሪቱ የተቀበለችውና የፈረመቻቸው ደንቦች የአገሪቱ ህግ አካል ተደርገው እንደሚወሰዱ ተገልጧል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስትም ለብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብት ልዩ ትኩረት መስጠቱ የታወቀ ነው። የተወሰኑ የአገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦችም የአንድ አካባቢ ተወላጅ/ባለቤት ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ብዙዎች የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የዓለም ዓቀፉ

የስራ ድርጅት እ.ኤ.አ በ1989 ባወጣው ስምምነት ቁጥር 169 ውስጥ በተገለጸው መሰረት የአንድ አካባቢ ተወላጅ/ባለቤት ህዝብ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት የህዝቦችን የጋራ መብትን የተቀበለ በመሆኑ ልዩ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባዋል፡፡ የጋራ መብት ዋነኛ የመገለጫ ባህሪም የህዝቡ ህብረትና አብሮ የመሆን አመለካከት ሲሆን ይህም በህገ መንግስቱ አንቀፅ 39(5) እውቅና ተሰጥቶታል፡፡

በኢፌድሪ ህገ መንግስት መሬት የህብረተሰቡ የጋራ ሃብት ለመሆኑ እውቅና በመሰጠቱ ህብረተሰቡ ለዘላቂ ልማት የሚኖረውን አስተዋጽኦ ያጎላዋል፡፡ የዚህ ህብረተሰብ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ዘዴ የጋራና ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ለብዝሃ ህይወት ጥበቃ ጉልህ አስዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛዎቹ የተፈጥሮ ደኖችና የብዝሃ ህይወት አካባቢዎች የአገሬው ህብረተሰብ መኖሪያ ስፍራ ጭምር ናቸው፡፡ በመሆኑም የህብረተሰቡን ባህላዊ መብትና የጋራ የመሬት ባለቤትነት መብቱን እውቅና መስጠትና መቀበል እነዚህን ቦታዎች ለትውልድ ለማቆየት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ትልቅ ስፍራ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ግን አንዳንድ በፌደራል ደረጃ የሚወጡ ህጎች በተወሰነ መልኩ በህገ መንግስቱ ከተቀመጡ መብቶች ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም፡፡ በፌደራል የመሬት አዋጅ አንቀፅ 2 (12) ንዑስ አንቀፅ 12 ስር በተጠቀሰው መሰረት የገጠር መሬትን ለአካባቢው ህብረተሰብ የመስጠት መብት የተሰጠው ለመንግስት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በህገ መንግስቱ ከተቀመጠው የማህበረሰቡ የመሬት ባለቤትነት መብት ጋር የሚቃረን ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ በግልፅ የተቀመጠው መንግስትና የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የመሬት ባለቤት መሆናቸው ነው፡፡

ሕገ መንግስቱ የመሬት ባለቤትነት መብትን በተመለከተ ከብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተለየ መብት ለመንግስት የሚሰጥ አይደለም፡፡ ሐቁ ይህ ቢሆንም የፌደራሉ የገጠር መሬት አዋጅ ግን እየተተገበረ ያለው ይህንን በሚፃረር ሁኔታ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የፌደራል ገጠር መሬት አዋጅ በዓለም ዓቀፉ የስራ ድርጅት

ስምምነት 169 ውስጥ የተጠቀሰውን የህብረተሰቡን ባለቤትነት መብት እንኳን ማካተት አልቻለም። በዚህ በዓለም ዓቀፉ የስራ ድርጅት ስምምነት 169 ውስጥ የመሬትና መሬቱ ላይ ያረፈው ማንኛውም ሃብት ባለቤትነት መብት እንዲጠበቅላቸው ተደንግጓል። በመሆኑም የአገሬው ነዋሪዎች በቀጥታ ባይዙትም ለተለያዩ የኑሮ ሁኔታዎች ሲጠቀሙበት የነበረ መሬት ካለ የባለቤትነት ወይም የመጠቀም መብታቸው ሊጠበቅላቸው ይገባል። ይህ የህዝቦች የመኖሪያ ክልል መብት ነው። ማለትም ከሰፈሩበት መሬት ውጭ በዙሪያቸው በሚገኘው መልከዓ ምድር ተራራና ወንዞች ላይ የሚኖራቸውን መብት ያጠቃልላል። የፌደራሉ የገጠር መሬት አዋጅን ጠለቅ ብለን ካየነው መንግስት ለአካባቢው ህብረተሰብ ለግጦሽ፣ ለደንና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጠው መሬት ወጥ የሆነ የመኖሪያ ክልልን ያቀፈ ሳይሆን የተበጣጠሰ መሬት ነው።

የፌደራል ደን ፖሊሲ አዋጅ ቁጥር 94/1986 የተመለከትን እንደሆነ ሦስት ዓይነት የደን ባለቤትነት መብቶች ተዘርዝረዋል። እነርሱም የመንግስት ደን፣ የክልል ደንና የግል ደን የሚባሉት ናቸው። የመንግስት ደን የሚባለው ከሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚሰጥ መመሪያ መሰረት የብዝሃ ህይወትንና የደን ስነ ምህዳሩን ጠብቆ ለማቆየትና ከጉዳት ለመከላከል ሲባል የሚከለልና ከአንድ ክልል ድንበር ውጭም ሊሆን የሚችል ደን ነው። ሆኖም ግን እስከ አሁን ድረስ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አስመልክቶ የወጣ መመሪያም ሆነ የተከለለ ቦታ የለም። በመሆኑም የትኛው ደን የፌደራል መንግስት የትኛው ደግሞ የክልሉ መንግስት እንደሆነ የሚያሳይ ነገር የለም።

የፌደራል የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1987 በግልፅ እንደሚያስቀምጠው ማንኛውም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ዕቅድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን ማካተት አለበት። ይህም ፕሮጀክቱ ከመተግበሩ በፊት በፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ወይም ውክልና በተሰጠው የክልል መንግስት መስሪያ ቤት በኩል በአግባቡ መገምገም ይኖርበታል። ሆኖም ግን በአቅም ማነስና ይህ

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አስፈላጊነት ተሻሽሎ በወጣው የኢንቨስትመንት አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 375/1998 ውስጥ በቂ ስፍራ ስላልተሰጠው በአፈፃፀም ረገድ ከፍተኛ ችግር በመታየት ላይ ነው።

የፌደራል አካባቢ ጥበቃም ቢሆን የሚቀርቡለትን የአካባቢ የተፅዕኖ ግምገማ ጥናቶች በጥልቀት መርምሮ ለማየት ያለው አቅም አጠያያቂ ነው። ባለስልጣኑ ይህን ለማድረግ የሚያስችለው ሰፋ ያለ አወቃቀር የለውም። በመርህ ደረጃ በኢንቨስተሮች ወይም በፕሮጀክቱ ባለቤቶች የሚዘጋጀውን አካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ለመገምገም ባለስልጣኑ መስራት ያለበት ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር ነው። ሆኖም ግን በአቅም ማነስ ምክንያት ባለስልጣኑ መስሪያ ቤቱ ከክልል የአካበቢ ጥበቃ ቢሮዎችና ከፌዴራል የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ጋር ተባብሮ የመስራት ሁኔታ ዝቅተኛ ነው።

የተሻሻለው ኢንቨስትመንት አዋጅ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ህጉን ለልማት አመቺ ያልሆነ አሰራር አደርጎ ነው የወሰደው። በዚህም ምክንያት የአካባቢ የተፅዕኖ ግምገማው አፈጻፀም ስርዓት የተገላቢጦሽ ሆኖ ይታያል። ይህም ማለት የኢንቨስትመንት ኮሚሽኑ ወይም የክልል የኢንቨስትመንት ቢሮም ሆነ ሌላ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሰጪ መስሪያ ቤት ፈቃድ ከሰጠ በኂላ ነው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማም ሆነ ሌላ ክትትል ለሚያደርገው የመንግስት አካል ማሳወቅ ያለበት። ይህ በመሆኑ በተግባር ሲታይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ማካሄድ ለአንድ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት መተግበር እንደ ቅድመ ሁኔታ በመታየት ላይ አይደለም።

ወደ ክልል ደረጃ ስንወርድም ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ግንኙነት ያላቸው ህጎች በአብዛኛው ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም። ለምሳሌ ያህል የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ህግ አዋጅ ቁጥር 53/2003 ብንመለከት የመንግስት ይዞታ የሆነን

መሬት ሲያብራራ በመንግስት የተከለለና የተያዘ መሬት ሆኖ ሰፋፊ የደን መሬቶችን፣ የዱር እንስሳትን፣ ፓርኮችን፣ ማዕድናትን ሃይቆችንና ወንዞችን ያጠቃልላል ይላል። ይህ ማለት እንግዲህ በአብዛኛው ጠቃሚ የሆነው መሬት በመንግስት የተያዘው ሲሆን ለነዋሪው ህብረተሰብ የሚቀረው ከአርብቶ አደሩ አካባቢ ከሚገኘውና የተለያየ ጥቅም የሚውለው ካልሆነ በስተቀር የተበጣጠሰ መሬት ነው። ይህ ደግሞ የህብረተሰቡን የመሬት ባለቤትነትን አስመልክቶ በሕገ መንግስቱም ሆነ እንደ የዓለም ዓቀፍ ስራ ድርጅት ስምምነት 169 የመሳሰሉ ዓለም ዓቀፍ ህጎች ከተቀመጠው አሰራር ውጭ ነው። የደ/ብ/ብ/ህ ብሔራዊ ክልል የመሬት አስተዳደር አዋጅም ህብረተሰቡ በመኖሪያ ክልሉ ውስጥ በሚገኝ መሬት ላይ የባለቤትነት መብት እንዳለው ያገናዘበ አይደለም። በተመሳሳይ መልኩ የክልሉ የደን አስተዳደር ልማትና ጥበቃ አዋጅም (አዋጅ ቁጥር 77/1996) ከኦሮሚያ ክልል የደን አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 72/1995) ጋር ሲነፃፀር ለማህበረሰቡ ደን የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነው።

በዚህ ጥናት እንደታየው ከሆነ በሸካ ዞን የሚታየው ተቋማዊ አወቃቀር በደንብ የተደራጀ ባለመሆኑ ለኢንቨስተሮች በሚሰጥ መሬት ላይ ውሳኔ ሲደረግ ህዝቡም ተሳታፊ እንዲሆን የሚያደርግ አይደለም። በተግባር እየታየ ያለው አሰራርና የተቋማቱ ተግባርና ኃላፊነት የሚጣጣም አይደለም። ምንም እንኳን የክልሉ ሕገ መንግስት ዋነኛ የሆኑ መብቶችን ከስር ላሉ የስልጣን አካላት የሚሰጥ ቢሆንም በሸካ ዞን ስር የሚገኙ የወረዳ አስተዳደሮች ግን በዞን ደረጃ የሚተላለፍ ውሳኔን ከማስፈፀም ያለፈ እንቅስቃሴ የላቸውም። ለምሳሌ ያህል ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ የእነዚህ ወረዳዎች ሚና የኢንቨስተሩን ደህንነትና የስራ እንቅስቃሴ ከማስጠበቅ ያለፈ አይደለም። በአጠቃላይ ከታች በሚገኙ የስልጣን እርከን ደረጃ የሚታየው ችግር የተቋማቱ ተግባርና ኃላፊነት የተመሰቃቀለና ግልጽነት የጎደለው ከመሆኑ የተነሳ ነው።

## 5.5. ከሸካ ደን የሚገኘው ጥቅም/እሴት

በዚህ ክፍል ከሸካ ደን ሊገኝ የሚችለውን አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ (Total Economic Value) ለመገመት ጥረት ተደርጓል፡፡ የአንድን ደን አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለመገመት በቅድሚያ ከደኑ የሚገኙት እሴቶች ጥቅም ላይ በመዋል ላይ የሚገኙ (Use Values) እና ገና ጥቅም ላይ ያልዋሉ (Non-use Values) በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉት እሴቶች እንደገና ቀጥተኛ ጥቅም ሰጪ (Direct Use Values) እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ሰጪ እሴቶች (Indirect Use Values) በመባል ለሁለት ይከፈላሉ፡፡ ጥቅም ላይ ያልዋሉት እሴቶችም እስከ አሁን ጥቅም ላይ ያልዋሉ ነገር ግን ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ፣ ተጠብቀው ለሚቀጥለው ትወልድ መተላለፍ ያለባቸው እና በሰው ሳይነኩ በተፈጥሮ እንዳሉ መቆየት ያለባቸው እሴቶች በመባል ለሶስት ይከፈላሉ፡፡ በአጠቃላይ የአንድ የተፈጥሮ ደን አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ/ዋጋ የሚለካው ሰዎች እሴቶቹን በመጠቀም ሊያገኙ በሚችሉት የገንዘብ መጠንና ደኑ ተጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ ባለድርሻ አካላቱ ለመክፈል በሚስማሙበት የገንዘብ መጠን ነው፡፡

የሸካን ደን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ/ዋጋ ለመገመት የተካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው ከሆነ ለናሙና ከተወሰዱት ቤተሰቦች መካከል በአማካይ 44 በመቶ ያህል የሚሆኑት ገቢያቸውን የሚያገኙት ከደኑና ከደን ውጤቶች መሆኑ ታውቋል፡፡ ከተፈጥሮ ደኑ በቀጥታ ሊገኙ በሚችሉ ጠቀሜታዎች ማለትም የቤት ግንባታ፣ የቤት ቁሳቁስ መስሪያ፣ የእርሻ መሳሪያና የአጥር ግንባታ የመሳሰሉት አጠቃላይ ዋጋ በዓመት በአንድ ሄክታር እስከ ብር 89 እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አሁን በሚታየው የአጠቃቀም ሁኔታ ጣውላ ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች ዋጋ በአንድ ሄክታር ከብር 1,192 እስከ ብር 8,142 እንደሚደርስ ይገመታል፡፡ በአንድ ሄክታር የተገመተው ይህ የገንዘብ መጠን በአጠቃላይ ደን መጠን ሲሰላ በባህላዊው የአመራረት አጠቃቀም ዘዴ የሚገኘው የአጠቃላዩ ደን ጣውላ ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች

ገንዘብ መጠን ለሻይ ተክል ልማት ከተሰጠው መሬት ከሚገኘው የተጣራ ገንዘብ መጠን ጋር ሲነጻጸር በሁለት እጥፍ ብልጫ እንዳለው ታውቋል፡፡

በሸካ የሚገኘው የቀርከሃ ደን መጠን ወደ 13,552 ሄክታር የሚደርስ መሬት ላይ የሚገኝ ሲሆን አንድ ሄክታር መሬት ከ100,000 እስከ 150,000 የሚደርስ የቀርከሃ ተክል ሊይዝ ይችላል፡፡ ቀርከሃን ለቤት፣ ለአጥርና ለንብ ቀፎ መስሪያነት ለአራት ዓመታት መጠበቅ አስፈላጊ ቢሆንና የአንድ የደረሰ ቀርከሃ ዋጋ ሁለት ብር ሆኖ በአጠቃላይ የማምረቻ ወጪው ሀያ በመቶ የሚደርስ ቢሆንና ዘላቂነት ባለው መንገድ መጠቀም ቢቻል በጠቅላላ ከሸካ የቀርከሃ ደን ሊገኝ የሚችለው ዓመታዊ የገንዘብ መጠን ከብር 542 እስከ 813 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል፡፡

ሌላው በዚህ ጥናት የታየው ትልቅ ጉዳይ የሸካ ደን ካርቦን የተባለውን ጋዝ አከማችቶ የመያዝ ጥቅሙን ነው፡፡ በአንድ ሄክታር ከሰው ንክኪ ነጻ ከሆነ ደን ወደ 280 ቶን የሚጠጋ ካርቦን እንደሚከማች ሲገመት ተቆርጦ ዳግም ያደገ ደን 194 ቶን ሲሆን ከገላጣ ደን ደግሞ 115 ቶን ካርቦን በአንድ ሄክታር ማከማቸት እንደሚችሉ ታውቋል፡፡ በሌላ በኩል አንድን የደን መሬት ለእርሻ ወይም ለግጦሽ ስናውለው ከ29 እስከ 38 ቶን የሚደርስ ካርቦን እናጣለን፡፡ ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነጻ የነበረ አንድ ሄክታር የደን መሬት ወደ እርሻ ማሳነት ቢቀየር እስከ 200 ቶን የሚደርስ ካርቦን ወደ አየር ይለቀቃል፡፡

የአንድ ቶን ካርቦን ዋጋ 10 የአሜሪካን ዶላር ቢሆን በዚህ ስሌት መሰረት የሸካ ደን ካርቦን የማከማቸት አቅሙ እስከ ብር 1.6 ቢሊዮን ሊደርስ እንደሚችል ይገመታል፡፡ እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ የተፈጥሮ ደን ካርቦንን አከማችቶ በመያዙ ሊገኝ የሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እውን ሊሆን የሚችለው ደኑ በአግባቡ ከተጠበቀ ብቻ ነው፡፡ በሌላ በኩል የሸካ የተፈጥሮ ደን ወደ ቡና ወይም ሻይ ተክል ልማት ሲቀየር በካርቦን ክምችት ከሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንፃር ሲታይ በአንድ ሄክታር

ከብር 3,4000 እስከ ብር 17,425 የሚደርስ ገንዘብ እናጣለን ማለት ነው።

## 6. ማጠቃለያ

አንጻራዊ በሆነ መልኩ በአገራችን ኢትዮጵያ ጥሩ የደን ሽፋን ከሚገኝባቸው ጥቂት ቦታዎች መካከል የሸካ ዞን አንደኛው ነው። በአሁኑ ሰዓት ከዞኑ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት ውስጥ 47 በመቶ ያህሉ በደን የተሸፈነ እንደሆነ ይገመታል። ሆኖም ግን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተባባሰ በመጣው የደን ውድመት ሳቢያ የደኑ ብዝሃ ህይወትና የአካባቢው ስነ-ምህዳር ለረዥም ጊዜ ተጠብቀው የቆዩ አካባቢዎችና የህብረተሰቡ የኑሮ ሁኔታ ለችግር በመጋለጥ ላይ ይገኛል። በዚህ ደን ውስጥ የተለያየ ጥቅም የሚሰጡ በርካታ የዕፀዋት ዝርያዎች ይገኛሉ። የአካባቢው ህብረተሰብ እንደ ማር፣ ቅመማ ቅመም፣ መድሃኒት፣ ምግብ፣ የከብት መኖ ወዘተ የመሳሰሉ ጣውላ ነክ ያልሆኑትን የደን ውጤቶች የሚያገኘው ከደኑ ነው።

ህብረተሰቡ ከደኑ ጋር ያለው ከፍተኛ ቁርኝት ለደኑ ለረዥም ጊዜ ተጠብቆ መቆየት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እንዳደረገ ይታመናል። የሸካ ዞን ህብረተሰብ አካባቢንና የተፈጥሮ ሃብትን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚረዱ ጠንካራ ማህበራዊ አደራጀጀት፣ ባህላዊ አሰራሮች፣ አስተዳደራዊ ደንቦችና የእምነት ስርዓቶች አሉት። ከዚህ በተጨማሪም የደን ወይም የዛፍ ባለቤትነት ባህላዊ ስርዓት በመኖሩና ይህም ለልጅ የሚተላለፍ ሃብት በመሆኑ ለደኑ ተጠብቆ መቆየት የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመምጣት ላይ ያለው የደን ውድመት ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል የህብረተሰቡ ባህል መቀያየር፣ በአካባቢው እየተስፋፋ የመጣው አንዳንድ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴና መንግስት የሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ሕጎች የሚፈጥሩት ክፍተቶች ተጠቃሽ ናቸው። በአብዛኛው የባህል ለውጥ ሊከሰት የቻለው የህብረተሰቡ እምነት ስርዓት ከመለወጡና በሰፈራ እና በሻይ ወይም በቡና ተክል ልማቱ ተቀጥረው ከሌላ ቦታ የሚመጡ ሰዎች እየተበራከቱ

ከመምጣቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ በክርስትና ሃይማኖት መስፋፋት ምክንያት የህብረተሰቡ ልማዳዊ የደን አጠባበቅ ስርዓትም ሆነ ለባህል መድሃኒትነት የመጠቀሙ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ ሊመጣ ችሏል፡፡ በከተማ አካባቢ ያለው ህዝብ ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ቀድሞ በአንድ ማህበረሰብ ብቻ ይፈጸም የነበረው የማገዶ እንጨትን ለገበያ ማቅረብ አሁን በስፋት እየተለመደ ሊመጣ ችሏል፡፡

በመንግስት የሚወጡ ፖሊሲዎችና ህጎችም ቢሆኑ ህብረተሰቡን በደኑ የመጠቀምና የመጠበቅ መብቱን አሳጥተውታል፡፡ ለእምነት ስርዓት ማካሄጃና ለቀብር ይጠቀሙበት የነበረውም ስፍራ በመንግስት ይዞታነት ተይዟል፡፡ ቀደም ሲል በግለሰቦች ይዞታ ስር የነበሩ ለማር እና ሌሎች ጣውላ ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች መገኛ የነበሩ የደን ስፍራዎችም ህዝቡ ባልተስማማበት ሁኔታ ለቡናና ሻይ ልማት ኢንቨስትመንት ሊሰጡ ችለዋል፡፡

ቆቦ በመባል የሚታወቁ የሰፋፊ ደን ባለቤት ግለሰቦችም የተደረገላቸው ካሳ ክፍያ አልነበረም፡፡ በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ፖሊሲዎች በህገ መንግስቱ እንዲሁም ደግሞ በአንዳንድ ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ውስጥ የተቀመጡትን የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦችን መብት ማስጠበቅ አልቻሉም፡፡ እንደ ፌደራሉ መሬት አዋጅና የክልሎች ገጠር መሬትና አጠቃቀም ህጎች የመሳሰሉት የተወሰኑ የፌደራልና የክልል ህጎችም በህገመንግስቱ ብሎም በአንዳንድ ዓለም ዓቀፍ ድንጋጌዎች የተቀመጡ የህዘቦችን መብት የሚያከብሩ ሆነው አልተገኙም፡፡ እነዚህ አዋጆች መንግስትን ብቸኛ የመሬት ባለቤትና ሲፈልግ መሬት መስጠት፣ መንጠቅና ለሌላ ማስተላለፍ የሚችል አካል አድርገውታል፡፡ ሆኖም ግን በሕገ መንግስቱ በግልፅ እንደተቀመጠው መሬት የመንግስትና፣ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሃብት ነው እንጂ ለመንግስት የተለየ የባለቤትነት መብት የሚሰጥ አይደለም፡፡ የተሻሻለውን የኢንቨስትመንት አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 375/87) የመሳሰሉት የተወሰኑ አዋጆችን ስናይም የራሳቸው ድክመት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል የተሻሻለው የኢንቨስትመንት አዋጅ ቀደም ብሎ ለወጣው ለአካባቢ

ተፅዕኖ ግምገማ ድንጋጌ (አዋጅ ቁጥር 299/87) ቦታ የሚሰጥ አይደለም፡፡

በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጁ ማንኛውም የኢንቨስትመንት እቅድ የአካባቢ ግምገማ ሪፖርት ማካተት እንዳለበት የሚያስገድድና ኢንቨስትመንቱ ከመተግበሩ በፊት ሪፖርቱ በፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንና ውክልና በተሰጣቸው የክልል የመንግስት አካላት በደንብ መታየት እንዳለበት የሚያስገድድ ነው፡፡ ሆኖም ግን ተሻሽሎ በወጣው የኢንቨስትመንት አዋጅ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መደረግ ያለበት ኢንቨስትመንቱ ከመተግበሩ በፊት ሳይሆን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለስልጣን ወይም የክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎች የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ከሰጡ በኋላ ነው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሪፖርቱን ለሚያየው የመንግስት አካል የሚያሳውቁት፡፡ አስፈፃሚ ተቋማቱ ከእነዚህ ፖሊሲዎችና ማህበራዊ ችግሮች ጎን ለጎን በደንብ ያልተደራጁና ብቃታቸው አነስተኛ በመሆኑ የወጡትን ፖሊሲዎችና ህጎች በአግባቡ ለማስፈፀም የሚችሉ አይደሉም፡፡ የተቋማት ተግባርና ኃላፊነትም አለመጣጣም ሌላው ችግር ነው፡፡ የተቋማቱ አወቃቀር ደካማ ከመሆኑ የተነሳ የሚደረገው ክትትል በቂ ስላልሆነ ትላልቅ የደን ስፍራዎችን ለኢንቨስትመንት የተረከቡ እንደ ኢስት አፍሪካ የሻይ ተክል ልማት የመሳሰሉ ኩባንያዎች ከተሰጣቸው ድንበር አልፈው ደኑን በመመንጠር ቀደም ሲል በህብረተሰቡ ጥበቃ ይደረግላቸው ወደ ነበሩ ውሃ አዘልና የወንዝ ዳር ደን ስፍራዎች ዘልቀው በመግባት ላይ ይገኛሉ፡፡

## 7. የመፍትሄ ሃሳቦች/አቅጣጫዎች

በሸካ ዞን ላይ የተደረጉት እነዚህ ዘርፈ ብዙ ጥናቶች ለወደፊቱ መወሰድ ያለበትን እርምጃ በማስመልከት የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦች አስቀምጠዋል፡-

1. በአካባቢው ያሉትን የደን ስፍራዎች በሚኖራቸው ስነ-ምህዳራዊ ዘለቄታነት፣ በሚሰጡት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና ለማህበራዊ

ፍትህ መስፈን በሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ላይ በመመስረት ድንበራቸውን መከለል፤

2. የአካባቢውን ነዋሪ ህብረተሰብ የመሬት ባለቤትነት መብቱን፣ በደኑ ላይ የተመሰረተውን የአኗኗር ዘይቤዎችንና ለባህላዊው የደን ጥበቃ ዘዴ አስፈላጊውን ዕውቅና መስጠት፡፡ እነዚህም ጉዳዮች በፌደራልና በክልል ደረጃ በሚወጡ ሕጎች ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ፤

3. ከማገዶ ፍጆታ ጋር በተያያዘ እየደረሰ ያለውን የደን ውድመት ለመቀነስ ይቻል ዘንድ አማራጭ የኃይል ምንጮችንና የገቢ ማግኛ ዘዴዎችን ማስፋፋት፤

4. ህብረተሰቡ በመሬትና በአካባቢ ላይ ያለውን መብት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በፌደራልና በክልል ደረጃ የወጡ ፖሊሲዎችንና ህጎችን በማሻሻል ከሕገ መንግስቱ ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ፤

5. የአካባቢው ህብረተሰብና ተቋማት የአካባቢውን ደን በመጠበቅና በመንከባከብ ረገድ በሕገ መንግስቱ የተሰጣቸውን መብት ማክበር፤

6. የኢንቨስትመንት፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና የወንጀለኛ መቅጫ ህጎች የማይይጣጣሙበትን ክፍሎች ለይቶ ማውጣት፤

7. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ህጉን ተግባራዊ ማድረግና የማስፈጸም አቅምን ማጎልበት፡፡ ከኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት ቀድሞ መደረግ ያለበት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው የኢንቨስትመንት ፈቃዱ በሚሰጥበት አካባቢ ያለውን ህብረተሰብ እሽታ እንደ ቅድመ ሁኔታ እንዲያካትት ማድረግ፤

8. ፈቃድ አግኝተው ስራ የጀመሩ የኢንቨስመንት ፕሮጀክቶችም ላይ ክትትል ማድረግና ተመሳሳይ ጉዳት እንዳይደርስ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፤

9. በአካባቢ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉት ጉዳት ዝቅተኛ የሆነና በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያላቸውን እንደ ኢኮ ቱሪዝም፣ የማርና የቅመማ ቅመም ምርት ለመሳሰሉ ኢንቨስመንቶች ቅድሚያ መስጠት የሚሉት ናቸው።